# ምሕረት ለማ? ለምን? እንዴት?

ተኮላ መኮንን
*Tekola Mekonen*
t.mekonen@verizon.net

ሰሞኑን በተለያየ የመገናኛ ማሰራጫዎች እየተሰማ ያለ ነገር ቢኖር እርቅ፤ ምሕረት የሚሉ ተደጋጋሚ ቃላቶች ሆነው አገኘኋቸው። "ይቅርታን የማይቀበል ግለሰብ ደካማ ሰው ብቻ ነው" የሚለውን በመፍራት ብዙዎች ከመናገር እየተቆጠቡ እንዳለ ሁሉ፡ ምንድነው የምታወሩት? እያሉ ተቃውሟቸውን የሚያሰሙ ታዋቂ ግለሰቦች መነሳታቸውን ሳይ ደግሞ ልቤ በተስፋ ተሞላ። ሁላችሁም እንዳነበባችሁትና እንደሰማችሁት ኢትዮጵያ ውስት በዘብጥያ ነዋሪ እንዲሆኑ የተደረጉት፤ ገሚሶቹ በሕዝብ ጭፍጨፋ ወንጀለኛነታቸው ተረጋግጦ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው የቀድሞ የደርግ ባለሥልጣናት ምሕረት ይደረግላቸው ተብሎ የተጀመረው እንቅስቃሴ አነጋጋሪ እየሆነ ነው። እንቅስቃሴውን የጀመሩት የተለያየ የሃይማኖት ድርጅት መሪ የሆኑ መንፈሳዊ አባቶች መሆናቸው ደግሞ ገሚሱን ከመናገር እንዲቆጠብ ያደረገው ይመስለኛል።

በግሌ ይቅርታ ሲነሳ የማስታውሰው "ነፍሱን ይማረውና" የጥላሁን ገሰሰን ዘፈን ነው።

ይቅርታ ምንድ ነው? ካልተስተካከለ

እሾህ አሜኬላ ሆድ እያበቀለ ................

የልብን ሰርቶ ይቅር በሉኝ

ምንስ አጠፋሁ ምን በደልኩኝ

በማለት አሉ ሰውን የሚያሞኙ............................

የሚለው ዘፈኑ ትዝ ይላችኋል። ጥላሁን ይህንን ሲል ይቅርታን መቃወሙ አልነበረም። ለይቅርታም አግባብ አለው ለማለት እንጂ። የግልን ጥቅም ለማራመድ የሚደረግ ይቅርታ ይቅርታ ሳይሆን ለበጣ ነው ማለቱም ነበር። እኔ በጣም የሚገርመኝ የትላንትና የኮሚኒስት መሪዎቻችን መጻጸት ሳይሆን ከቀዩ ደብተር ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ ማንሳታቸው ነው። ወንድሞቼ ሰው ይቀየራል የሚቀየረው ግን ሌላውን ለማሞኘት ሲሆን ያናድደኛል። ትላንትና አስረዋቸው ይቅርታ ይደረግልን "አብዮቱን ተቀብለናል" ብለው የማሉላቸውን ወጣቶች የረሸኑ ባለስልጣናት ዛሬ ምሕረትን ጠየቁ ሲባል መታወስ ያለበት የነኛ ወጣቶች የደም እንባ ነው።

የነጻ እርምጃ ማለት ምን ማለት ነበር? ወንድሞቼና እህቶቼ። የመሰለህን ያልጣመህን የጠረጠርከውን "ጸር አብዮተኛ" ነው ያልከውን ያለፍርድ ግደለው ማለት አልነበረምን? እኛን የማይደግፈንን ሁሉ ግደል ማለት በሰብእ ላይ የተደፈጸመ ግፋዊ ወንጀል (CRIME AGENEST HUMANITY) ካልተባለ ምን ሊባል ነው? ማናቸውም ከኛ የማይገጥም የፖለቲካ ፓርቲ አባላትን አስወግድ ማለት ሕዝብን የማጥፋት ግድያ (GENOCIDE) ካልተባለ ምን ሊባል ነው? የገደልኩበትን ጥይት ካልከፈላችሁ አስከሬን አንሰጥም የሚል ቡድን ፋሽስት ካልተባለ ምን ሊባል ነው? ለሞተ ማዘን ክልክል ነው ብሎ በማወጁ አዋጁን

ጥሳችኋል ብሎ ሐዘንተኛን ያስር የነበረ ሁሉ በሰፈርከው ተሰፈረብህ ከማለት ሌላ ፍርዱን እግዚአብሔር ይስጣቸው ከተባለ ማሰርን ምን አመጣው? እስር ቤትስ ለምን አስፈለገ? ፍርድ ማለትስ ምን ማለት ነው?

እነዚህን የቀድሞ ባለሥልጣናት ጉዳይ እያጠኑ ብያኔ የሰጡትን ዳኞች በፍርዳቸው ሳንስማማ የተቀበልነው ብዙ እንዳለ መታወቅ ይኖርበታል። የተለቀቁ ወንጀለኞች እኮ እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ዳኞቹ በእስራት የፈረዱትን ፍርድ ይግባኝ ያለው አቃቢ ሕግ በሞት ያስቀየረው እኮ ሕግን ተከትሎ ነው። በከርከራቸው ወቅት ወፍ አልገደልንም ብለው ይመጻደቁ የነበሩ እነዚህ ባለሥልጣናት ዛሬ ማጠፊያው ሲያጥርባቸው የምሕረት በትር የእምነት ሽፋን ይዘው ቀረቡ።

ይቅርታ ጠያቂዎቹን መንፈሳዊ አባቶች የምንጠይቃቸው ነገር ቢኖር ትላንት ከሚሊዮን ያላነሳ ሕዝብ ሲጨፈጨፍ ዝም በማለታቸው መጀመሪያ እራሳቸው ሕዝብንም ፈጣሪንም ይቅርታ እንዲጠይቁ ነው። እንደግለሰብ ብዙ ዘመዶቼን በደርግ የፋሽስት መንግስት ግድያ አጥቻለሁ። የማርቆስ ተድላ የግፍ ደም የበለጠ መኮንን የግፍ ደም የግርማ ነጋሽ የግፍ ደም ጥቂቱ ነው። ደማቸውን መበቀል ባልችል እንኳን ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ እንዳይቀር በሕግ የመታገል ሃላፊነት አለብኝ እላለሁ።

ምሕረት ለምን አስፈለገ? ለሚለው እየተሰጠ ያለው መልስ ሰላምን ለመፍጠር ነው ሲባል ስሰማ ደግሞ ይበልጥ ያስገርመኛል። አገራችን ሰላም የሰፈነው እኮ እነዚህ ወንጀለኞች እስር ቤት በመግባታቸው ነው። ይህንን የሚክድ ይኖር ይሆን? ታዲያ ሰላም ተፈጥሮ እያለ ሰላምን ለማደፍረስ ካላሰብን በስተቀር ለምን ሕዝብን የሚያስቆጣ ነገር እንጀምራለን? በእኔ እምነት በአንድ ሃገር ሰላም የሚሰፍነው የዲሞክራሲያዊ መብት ሲረጋገጥ የሕግ የበላይነት ተቀባይነት ሲኖረው ብቻ ነው እላለሁ። የሕግ የበላይነት ተከበረ ማለት የሚቻለው ደግሞ ውሳኔው ተፈጻሚነት ሲኖረው ነው። ሕግ እኮ ባለፈ በተከሰተ ችግር ላይ ተመርኩዞ የተፈጠረው ችግር እንዳይደገም መከላከያ መሳሪያ ነው። ታዲያ በሕግ ሳይሆን በምሕረት ላይ የተመሰረተ ሃገር መፍጠር ከፈለግን ላለመስማማት ጅምር ድንጋይ እየተከልን ነው እላለሁ።

ከደርግ እስር ቤት ውስጥ 15 ዓመት እድሜ አሳልፎ የተፈታ አንድ ወንድሜ ያወጋኝን ላካፍላችሁ። በወቅቱ የፖለቲካ እስረኞች እስር ቤቱን ያጣበቡበት ሰዓት ነበር። ታዲያ አንድ ስማቸው "ለሰማይና ለምድር" የከበደ የደርግ ባለስልጣን እስር ቤት እስረኞችን ለመጎብኘት ይመጣሉ:: በወቅቱ ያገኙትን እስረኛ ሁሉ የታሰረበትን ወንጀል ሲጠይቁ ብዙው ወረቀት ስበትን ተገኝቼ፡ "ጸረ አብዮተኛ" ሆኜ: ተገንጣይ በመሆኔ፡ እያለ ሲመልስ አዳመጡና ፈንጠር ብሎ የቆመውን አንድ እስረኛ በወታደር አስጠርተው አንተስ ምን ወንጀል ፈጽመህ ታሰርክ? ብለው ባለሥልጣኑ ሲጠይቁት የመለሰው ምን ነበር መሰላችሁ "ጌታዬ የእኔ ወንጀል ቀላል ነፍስ ነው።" የሚል ነበር። እኔ በፖለቲካ ሳይሆን ነፍስ አጥፍቼ ነው የታሰርኩት ማለቱ ነው። ታዲያ በፖለቲካ ልዩነት የሚደረጉ ትግሎች ከነፍስ ግድያ የበለጠ ወንጀል እንደነበረ ሌሎች ወንጀለኞችም አውቀው እንደነበረ ነው አባባሉ የሚነግረን።

ሂትለር እስራኤላውያንን አልጨፈጨፈም ብለው የሚከራከሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ዛሬም እንዳሉ ሁሉ ደርግ አልገደለም የሚሉ ቢኖሩ መደነቅ አይኖርብንም። ሁለቱም በመሃከሉ ሊያራምዱት የሚፈልጉት የግል ጥቅም አላቸውና። በሕይወት ከሞት የተረፉ የደርግ እስረኞችን፡ ከሂትለር የማጎሪያ እስር ቤት (CONCETRATION CAMP) የተለቀቁ ግለሰቦችን የሕይወት ምስክርነት እያዳመጡ እንኳን አልሰማንም የሚሉ ግለሰቦችን ለማሳመን መከራከር ደግሞ ጊዜ ማጥፋት ይመስለኛል።

ባልሳሳት ትግራይ ውስጥ ይመስለኛል ሁለት ልጆቻቸው በደርግ ታስረውባቸው ስንቅ ማመላለስ የሰለቻቸው አባት አሳሪው ባለሥልጣን ቢሮ ድረስ ሄደው "እባክህ ስንቅ ማመላለስ ሰለቸኝ አንዳንድ እንካፈልና ስንቅ ከማቀበል ልገላገል" አሉ ይባል ነበር። አንዱን ምረጥና ግደለው አንዱን ፍታልኝ ማለታቸው ነበር። ሌላ መናገር ያስፈልግ ይሆን።

ሻለቃ መላኩ የእግዜር ታናሽ ወንድም

የዛሬን ማርልኝ መልሼስ አልወልድም።

ልጅ የወለዳችሁ መልሳችሁ ዋጡ

እኔ አላማረኝም ዓይን አገላለጡ።

ያለውን ሕዝብ ምንም አይደል እርሳው ሊሉ የተነሱ ዳግም እራሳቸውን ሊጠይቁ ይገባል። አሊ ሙሳ ያደረገውን አውቆ በራሱ ላይ ፈረደ። መላኩ ተፈራ ደግሞ ክርስቲያናዊ ልቡ ተከፈተና ይቅርታ ጠየቀ። ይህ በሕዝብ እንባ መቀለድ ይሆናል። ወንድሞችና እህቶች ክርስቶስ የይቅርታ አምላክ ነው ነገር ግን ከይቅርታ በላይ ሐጥያት ለሰሩ ገሃነመ እሳትን እንዳዘጋጀ አንርሳ።

በፈላ ዘይት በርሜል ውስጥ የነፈሩትን፣ በብልታቸው ጠርሙስ የተከተተባቸውን፣ ጣታቸው የተቆረጠ፣ ጥፍራቸው በወረንጦ የተነቀለውን። በግርፋት ሰውነታቸው ተልቶ የሞቱትን፣ በየመንገዱ የተረሸኑትን፣ አስቡና መሃሪው ማነው የሚማሩትስ እነማን ናቸው? ብላችሁ ጠይቁ። መልሱንም በራሳችሁ ለመመለስ ተዘጋጁ። ሁል ግዜ ምህረት ለማ? ለምን? እንዴት ብሎ መጠየቅም ብልህነት ነው። ለምሕረትም አይነትና ቦታ አለውና።

ትዝ ይላችሁ እንደሆን የሮማው ጳጳስ በእስራኤላውያን ላይ የተደረገውን ጭፍጨፋ በወቅቱ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ግድያውን ሳትቃወም በመቆየቷ ዘመናት ቢያልፉም እስራኤል ድረስ ሄደው ይቅርታ መጠየቃቸው ዜና ነበር። በተመሳሳይ የፋሽስቱን የጣልያንን ወታደር ባርከው ወደ ሃገራችን የላኩት የካቶሊክ መንፈሳዊ አባቶች የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንዲጠይቁ የሚያሳስብ ፊርማ በዓለም ዙሪያ ሲፈረም እንደነበርም ትዝ ይለኛል መፈረሜንም አስታውሳለሁ። ታዲያ ዛሬ ምሕረት ሊጠይቁ ለተነሱት አባቶች ያለኝ ጥያቄ ቢኖር በደርግ ዘመን ይደረግ የነበረውን ጭፍጨፋ በወቅቱ በገለልተኛነት በመመልከታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ዛሬ በቅድሚያ ይቅርታ መጠየቅ እንዳለባቸው ነው።

ሃገር በዲሞክራሲና በሕግ እንጂ በምሕረት አይተዳደርም።